**ተጨማሪ መረጃ፣**

**ስለ የሴት ግርዘት አስመልክቶ ለ የኖርወይ የጤና ባለሞያዎች የወጣ መምርያ ፣**
**(በመንግስታዊ ድርጅት፣ የጤና ጥበቃ የተዘጋጀ፥ ማዘዣ ቁጥር IK 2723)**
**ስለ በሴቶች ብልት ላይ ጉዳት ማድረስ አስመልክቶ የወጣ የአፈጻጸም ንድፍ፥** (ታህሳስ 11. 1993፣ ክየልጆችና የቤተ-ሰብ ሚኒስተር የቀረበ፥ ብተለፎን ቁጥር 22 24 24 07 ማዘዝ ይቻላል)

**የማስታወቅያ ትንሽ-ጽሑፍ**
**በማህበራዊና የጤና-ጥበቃ ሚኒስተር የተዘጋጀ**

**የመንግስት መስሪያ-ቤቶች ቀጥሎ ካለው አድራሻ በብዛት ማዘዝ ይችላሉ።**

Statens forvaltningstjeneste
Informasjonsforvaltning
Postboks 8169 Dep, 0034 OSLO
የፋክስ ቁ . 22 24 27 86
ኢ-መይል publikasjonsbestilling@ft.dep.no

ማዘዣ ቁጥር 1-1053 AM

# ስለ የሴቶች ብልት መጉዳት ሕግን አስመልክቶ የተዘጋጀ የማስታወቅያ ትንሽ ጽሑፍ

SOSIAL- OG HELSEDEPARTEMENTET

## በታህሣሥ 7 ቀን 1988 እ. ኢ. ኣ. ስለ የሴቶች ብልት ማበላሸት ኣስመልክቶ የወጣ ሕግ ቁ. 74.

§ 1. ሆን ብሎ የሴቶች ብልትን መጉዳት፡ ወይም በብልት ላይ ዘላቂ ለውጥ የሚያደርስ ቀዶ-ጥገና ማድረግ፥ በየሴት ብልትን ማበላሸት ሕግ ያስቀጣል። ቅጣቱም እስከ 3 ዓመት እስር ይሆናል። የደረሰው ጉዳት ሁለት ሣምንት የሚደርስ በሽታ ወይም የስራ ችሎታ ማነስ ያስከተለ ወይም ወደ ነበረበት ሊመለስ የማይችል የኣካል ጉዳት መዛባት ወይም መናጋት ከሆነ ግን ቅጣቱ እስለ 6 ዓመት የሚደርስ እስር ይሆናል። ጉዳቱ ሞት፥ ወይም በኣካል ወይም በጤንነት ላይ ታላቅ ጉዳት ያስከተለ ከሆነ ቅጣቱ እስከ 8 ዓመት የሚደርስ እስር ይሆናል። መተባበርም ላይ ከተጠቀሰው ደንብ መሰረት በተመሳሳይ ያስቀጣል።

የተጎዳውን የሴት ብልት እንደገና ጥገና ማድረግ በመጀምርያ ምዕራፍ በተጠቀሰው ሕግ መሰረት ያስቀጣል።

ብስምምነት ማድረግ ከቅጣት ኣያድንም።

§ 2. ይህ ሕግ ንጉሡ ከወሰነበት ቀን ጀምሮ ሥራ ይውላል። ከታህሳስ 23 ቀን 1988 እ. ኢ. ኣ. ጀምሮ ሥራ ላይ ውለዋል።

### የሕጉ ዓላማ፥

የሕጉን ዓላማ በኖርወይ በሴት ብልትን ጉዳት ማድረስ የተከለከለ መሆኑን ግልጽ ለማድረግ ነው። ሕጉ ሴት ልጆች እንዳይገረዙ ይከለክላል። የዚህ ዓይነት ቀዶ-ጥገና በሴቶች ብልት ላይ ማድረግ ለጤና ጠንቅ ስለ ሆነ፡ በኖርወይ ሕግ መሠረት ተቀባይነት የለውም። ግርዛት ሁሉም በኖርወይ የተከለከለ ነው። የሴት ብልትን በግርዛት ስም መጉዳት ኣስመልክቶ የራሱ የሆነ ሕግ ማውጣት ደግሞ መልእክቱን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል። ሕጉ የኖርወይ ስርዓት ብሴቶች ግርዛት ያለው ኣቋም ግልጽ መልእክት ነው።

### የሴት-ልጅ ብልት መጉዳት የሚል ፅንሰ-ሓሳብ፡

ሕጉ "የሴት-ልጅ ብልት መጉዳት" የሚለውን ፅንሰ-ሓሳብ ይጠቀማል። ይህን ፅንሰ-ሕሳብ በዓለም የጤና ድርጅትና ሌሎች ከሲህ የስራ መስክ የሚሰሩ ዓለም-ኣቀፍ ድርጅቶች ዘንድ በብዛት ይሰራበታል። (በእንግሊዝኛ Genital mutilation ይሰኛል)። ይህን ኣሰያየም ብሴት ብልት ላይ የሚደረግ ቀዶ-ጥገና ምን እንደምያስከትል ያሳያል። ፅንሰ-ሓስቡ የሴትን ብልት መግረዝ ብልሽት የሚያስከትል ድርጊት መሆኑ ያመለክታል። ስለሆነም በሴቶችን ብልት የመግረዝ ጉዳት ማድረስ ከወንዶች ግርዛት ተለይቶ ይታያል። የወንዶች ግርዛት የሃይማኖትና የእምነት ይዘት ያለው ሲሆን፡ በጢንነት ላይ የሚያስከትለውን የታወቀ ጉዳት የለውም።

### ሕጉ የሚመለከታቸው ቀዶ-ጥገናዎች የትኞች ናቸው?

ሕጉ በሴት ልጅ ብልት ላይ የሚደረጉ፡ ማለትም በሴቶች ብልት ላይ ጉዳት ወይም ዘለዓለማዊ ለውጥ የሚያስደርሱትን ቀዶ-ጥገናዎች ሁሉ ይከለክላል። ይህን ማለት ዘወትር የሚደረገው፡ የሴትን ብልት የተወሰነ ክፍል መቁረጥ ጀምሮ እስከ ቀዳዳውን መስፋትና በቀዶ-ጥገና የብልትዋን ክፍል (Clitoris) ብከፍልም ሆነ ሙሉ ብሙሉ መቁረጥን የተከለከለ መሆኑ ያመለክታል። እንዲሁም የመግቢያ ቀዳዳውን መልሶ መስፋት የተከለከለ ነው፥ ለምሳሌ ክወሊድ ብኃላ። ብሌላ በኩል ተፈጥሮኣዊ የሆነውን የኣካል ቅርጽ ለማግኘት የሚደረገውን ቀዶ-ጥገና ይፈቀዳል። ሕጉ በሕክምና የተደገፉ ቀዶ-ጥገናዎችን፥ ማለትም በወሊድ ጊዜና፡ በነቀርሳ በሽታ የተነሳ የሴትዋን ብልት የተወሰነ ክፍል ቆርጦ ማውጣትን ኣይገድብም። ኣብሮ የተወልደውን የባህርያዊ ቅርፅ ጉድለት ለማስተካከል ወይም በሕግ ተቀባይነት ያላቸው የጾታ መለወጥ የሚመለከቱ ቀዶ-ጥገናዎችም በዚህ ሕግ ኣይገደቡም።

### በዚህ ሕግ የሚከለከሉት እነማን ናቸው?

ሕጉ ማንኛውንም በሴት ብልት ግርዛት የሚያደርገውን ሁሉ ይመለከታል። በተጨማሪም ኣንድ ሰው ራሱ ቀዶ-ጥገና ባያደርግም፥ የሴት ልጅ ብልት ለመበላሸት መተባበር የተከለከለ ነው። ወላጆች ወይም ሌሎች፡ የሴት ልጅ እንድትገረዝ ኣስተዋጽኦ ካደረጉ ይቀጣሉ። ሴትዋ የስምምነት ቃል ብትሰጥም ሕጉ ተግባራዊ ይሆናል። ሴትዋ ራስዋ ግን ኣትቀጣም።

### በውጭ ኣገር የሚደረግ ቀዶ-ጥገና፡

ሕጉ በኖርወይም ሆነ በውጪ ኣገር የሚደረግ ግርዛት ይመለከታል። ይህም ሴት ልጅ ወደ ግርዛት የሚፈቅድበት ሌላ ኣገር ተውስዳ እንዳትገረዝ ይከለክላል። ስለሆነም በሴት ልጅ ብልት ጉዳት ማድረስ ማንኛውም የኖርወይ ዜጋም ሆነ በኖርወይ ነዋሪ የሆነ ሁሉ ድርጊቱን እንዳያደርግ/እንዳታደርግ ወይም ቀዶ-ጥገናው በውጪ ኣገር እንዲደረግ እንዳያደርጉ ይከለክላል።